An Oifig um Chosaint Idirnáisiúnta
International Protection Office

**የአመልካች የሥነ ምግባር ደንብ**

የዓለምአቀፍ ጥበቃ የመስመር ላይ

ቃለ መጠይቅዎን በተመለከተ መረጃ

በዚህ ግዛት ውስጥ ለዓለምአቀፍ ጥበቃ ጥያቄ እና የይገባኛል ጥያቄዎን በተመለከተ ለዚህ ጽህፈት ቤት መጠየቅ አቅርበዋል። የዓለምአቀፍ ጥበቃ የመስመር ላይ ቃለ መጠይቅ አላማው ቀድሞውኑ ከተሰጡት መረጃዎች እና በመስመር ላይ ቃለ መጠይቅዎ ላይ ከሚሰጡት መረጃዎች የእርስዎን የይገባኛል ጥያቄ ሙሉ ዝርዝሮችን መመርመር ነው። ይህ እርስዎ በጥያቄዎ ውስጥ ካነሱዋቸው ጉዳዮች እና ቃለ መጠይቅ አድራጊው አግባብነት እንዳለው ከሚያስቡት ሌሎች ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ዝርዝር ጥያቄን ይጠይቃል። ከቃለ መጠይቁ ጋር በተያያዘ ያልተረዱትን ጥያቄዎች ቃለ መጠይቅ አድራጊው ማብራሪያ እንዲሰጡዎ መጠየቅ አለብዎት።

ፍራቻዎን በግልጽ እና በትክክል ማስረዳት እና ከእርስዎ ልዩ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ ሁሉንም መረጃዎች እና ዝርዝሮች ማቅረብ አለብዎት። ቃለ መጠይቁ ወደ ትውልድ ሀገርዎ ለመመለስ ለምን እንደሚፈሩ በዝርዝር ለማስረዳት እድል ይሰጥዎታል።

**ሙሉ በሙሉ መተባበር እና ሙሉ በሙሉ ሀቀኛ መሆን ግዴታዎ** ነው። የመስመር ላይ ቃለ መጠይቁ በቃለ መጠይቅ አድራጊውዎ አማካኝነት በይገባኛል ጥያቄዎ ላይ አግባብነት ያላቸውን እና አግባብነት ሊኖራቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በጽሑፍ ያስቀምጣል። የቃለ መጠይቁ መዝገብ በመስመር ላይ ቃለ መጠይቁ ወቅት ይነበብልዎታል እና የጊዜ ማኅተም ይደረግበታል እናም ይህ በትክክል አልተመዘገበም ብለው የሚያስቡትን ማንኛውንም ዝርዝር ለማስተካከል እድል ይሰጥዎታል። በቃለ መጠይቁ ወቅት ከቃለ መጠይቁ መዝገብ ጋር መስማማትዎን በቃል እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ እናም ይህ በመዝገቡ ላይ የጊዜ ማኅተም ይደረግበታል። የጊዜ ማኅተም የቃል ማረጋገጫዎን እና የዚህን ጊዜ/ቀን ያሳያል።

የዓለም አቀፍ ጥበቃ ቢሮ በምንም ዓይነት ሁኔታ እርስዎ ከሚሸሹበት ሀገር ባለሥልጣናት ጋር አይገናኝም።

ቃለ መጠይቁን ተከትሎ ከማመልከቻዎ ጋር በተያያዘ ምክር ይሰጣል እና ይህ ምክር አሉታዊ ከሆነ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማለት እድል ይኖርዎታል።

**<u>የአስተርጓሚው ሚና፦</u>** አስተርጓሚው በቦታው የሚገኝ ከሆነ የቃለ መጠይቅ አድራጊውን ጥያቄዎች እና የእርስዎን ምላሾች በትክክል ይተረጉማል። አስተርጓሚው ለእርስዎ ምክር አይሰጥዎትም ወይም እሱ/እሷ በጉዳይዎ ጠቀሜታ ላይ ማንኛውንም አስተያየት አይሰጥም። አስተርጓሚው የቃለ መጠይቁን ሚስጥራዊነት ያውቃል አስተርጓሚው በቃለ መጠይቅ አድራጊው በኩል ካልሆነ በስተቀር ከእርስዎ ጋር ውይይት ውስጥ መግባት አይፈቀድለትም።

**<u>የህግ ተወካይ፦</u>** ህጋዊ ተወካይዎ በቦታው ካለ ማስታወሻ ሊወስድ ይችላል ነገር ግን ሊያቋርጥዎ ወይም ማንኛውንም ጥያቄ ሊመልስዎ አይችልም። በቃለ መጠይቁ ማብቂያ ላይ ህጋዊ ተወካይዎ እሱ/እሷ አስተያየት እንዲሰጥ ይጠየቃል።

በቃለ መጠይቅዎ መጀመሪያ ላይ ይህንን ሰነድ እንዳነበቡ እና እንደተረዱት እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ።

**የአመልካች ስም፦**

**የተስማሙበት ቀን፦ ቀን/ወር/ዓመት** **የተስማሙበት ሰዓት፦ ቀን/ወር/ዓመት**